**Kinijit North America Association of Support Organizations (KNAASO)**

766 Rock Creek Church Rd., NW. Washington DC, 20010

Telephone: (202) 541-0556. FAX: (202) 541-0557. kinijitna@kinjitna.org

www.kinijitna.org


## የቅንጅት ሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር 4ኛ ጠቅላላ ጉባዔ የአቋም መግለጫ

የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቱ የሚከበርባት፤ መልካም አስተዳደርና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመገንባት ያለውን ቁርጠኝነት በግንቦት 1997 ዓ.ም ምርጫ ወቅት በምርጫ ካርዱ አማካይነት አረጋግጧል። ይህንን ታሪካዊ ወር መሠረት አድርጎ የተካሄደው 4ኛው ጠቅላላ ጉባኤያችን በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን አሳሳቢ ጉዳዮች ከመረመረና በሰሜን አሜሪካ የሚገኙት የድጋፍ ድርጅቶች ውጤታማነታቸውን ይበልጥ በሚያጎለብቱባትን ሁኔታ በጥሞና ካጠና በኋላ የሚከተሉትን የአቋም መግለጫዎችና ውሳኔዎች አሳልፏል።

1ኛ - በ 1997 ዓ/ም ምርጫ በሕዝብ የተመረጡት የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ መሪዎች፤ እንዲሁም ሌሎች የዲሞክራሲ ታጋዮች፤ የፈጠራ ክስ ተመስርቶባቸው እንዲንገላቱ መደረጉ የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ ሳይሆን መላውን ዓለም ያሳዘነ ሕገወጥ ድርጊት ስለሆነ ያለአንዳች ሁኔታ እንዲፈቱ ጥሪያችንን በድጋሜ እናስተላልፋለን። የመሪዎቹን መፈታት እውን ለማድረግ በሃገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደርጃ የሚከናወኑ ጥረቶችን እንደግፋለን።

2ኛ - መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እየደረሰበት ያለውን አፈናና የመሰረታዊ መብቶች መገፈፍ በፅኑ እያወገዝን፤ ህዝባችን በየዘርፉ የሚያካሂደው ሰላማዊ ትግል ይበልጥ ጥራት ባለው መንገድ እንዲመራ የሚያስችሉ ስልቶችን በማዘጋጀት በኩል አስፈላጊውን አስተዋጻኦ እናደርጋለን።

3ኛ - የኢትዮጵያ መንግሥት ወታደሮቹን ወደሶማሊያ ምድር ማስገባቱ የአፍሪቃ ቀንድን የፖለቲካ ሁኔታ ከምንጊዜም የበለጠ ውስብስብ የሚያደርግና በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ጥቅምና ደህንነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚኖረው አንጠራጠርም። በዚህ ረገድ የሃገሩን ዳር ድንበር የማስጠበቅ አደራ የተቀበለው የኢትዮጵያ ሠራዊት አስፈላጊ ባልሆነ ጊዜና ቦታ ደሙ መፍሰሱን አጥብቀን እንቃወማለን። ስለሆነም ሠራዊታችን ከሶማሊያ ምድር በአስቸኳይ እንዲወጣና ኢትዮጵያም ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በአፍሪካ ቀንድ ሠላምን ለማስፈን በሚያደርገው ጥረት ውስጥ ብቻ እንድትሳተፍ እንጠይቃለን።

4ኛ - የሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ዲሞክራሲያዊ መሠረት እንዲኖራቸውና አሠራራቸው ግልጽነትና ተጠያቂነት ኖሮት ያካባቢያቸውን ሕብረተሰብ ተሳትፎና ተአምኖ እንዲያገኙ በማድረግ ረገድ በመወሰድ ላይ ያለው ርምጃ ይበልጥ እንዲፋጠን ወስነናል። ከቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ጋር ያለው አሠራርና ግንኙነትም ሥራን የሚያቀላጥፍና ውጤታማነትን ያማከለ እንዲሆን ወስነናል።

5ኛ - የዲሞክራሲ ትግሉ ዕምብርት ሃገር ቤት ውስጥ እንደመሆኑ መጠን ቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ይህንኑ ሠላማዊ ትግል በማገዝ በኩል የሚወስዳቸው ርምጃዎች ከምንጊዜውም የበለጠ ተጨባጭ እንዲሆኑ እናሳስባለን።

6ኛ - ከቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶችና ከዓለም አቀፍ አመራሩ ራሳቸውን ያገለሉ አንዳንድ ግለሰቦች የቅንጅትን ስምና ዓርማ ሃላፊነት በጎደለው መልክ እንደግል ንብረታቸው ማስመዝገባቸው እጅግ በጣም አሳዝኖናል። እነዚህ ግለሰቦች በኢትዮጵያ ሕዝብ ሠላማዊ ትግል ውስጥ ከፍተኛ ሚና በመጫዎት ላይ የሚገኙትን የድጋፍ ድርጅቶች እንቅስቃሴ ለማሰናከል የወሰዱትን እርምጃ መሪዎቻችን እንደሚያወግዙት በማመን ቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር የሚወስደውን ሕጋዊ ርምጃ በሚያስፈልገው ሁሉ እንረዳለን።

7ኛ - በቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር ውስጥ የተከሰተውን ችግር በውይይት ለመፍታት ቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራርና የድጋፍ ድርጅቶቹ ያሳዩትን ፈቃደኝነትና ትዕግስት እናደንቃለን። ይሁን እንጅ ይህ ችግር መቋጫ እንዳያገኝ በሚፈልጉ ግለሰቦች ሴራ ምክንያት ሠላማዊ ትግሉ ሊዳከም ስለማይገባ ህብረተሰቡ የሁኔታውን ጭብጥ የሚያገኝበት መድረክ እንዲፈጠር በዓለም አቀፍ አመራሩና በማሕበራችን በኩል አስቸኳይ እርምጃ እንዲወሰድ ወስነናል። በመረጃ እጥረት ምክንያት ራሳቸውን ከውጤታማ እንቅስቃሴ መሥመር ያራቁ ወገኖቻችን የቅንጅትን መርህ ተከትለን ከምንሠራው ድርጅቶች ጋር እጅ ለጅ እንድንያያዝ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

8ኛ - የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ማሕበርን ውጤታማነት እንዲያዳብሩ የተዘጋጁት መመሪያዎችና ያሳለፍናችው ውሳኔዎች በተግባር እንዲተረጎሙና በተለይም የሴቶችና የወጣቶችን ተሳትፎ የሚያጠናክሩት እቅዶች ልዩ ትኩረት እንደሰጣቸው ወስነናል።

7 - የኢትዮጵያ ሚሊኒየም ህዝባችን አዲስ የሠላምና የልማት ራዕይ የሚቀርጽበት፤ ታሪኩንና ባሕሉን የሚያወድስበት ልዩ አጋጣሚ መሆኑን እናምናለን። ይህ የታሪክ አጋጣሚ በከንቱ እንዳይባክንና መንግሥትም ሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ለአጭር ጊዜ የፖለቲካ ጥቅም ማራመጃ እንዳያውሉት የማድረግ ሃላፊነት እንዳለብን ማስገንዘብ እንወዳለን።

ቅንጅት የሰሜን አሜሪካ ድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር
4ኛ ጠቅላላ ጉባዔ
ዋሽንግተን ዲሲ
ሜይ 15፣ 2007